ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ.007
ጳግሜ 2017 ዓ.ም.



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኙነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

በኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

**BRIDGE** Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

+251 911 86 12 34
+251 115 57 74 96
research@bridge-et.org
https://bridge-et.org/
150096, Addis Ababa, Ethiopia.
Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.









# ማውጫ


የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ.................. 2

እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው....... 10

የብሪጅ ዓመታዊ አጭር ዳሰሳ................ 11

# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ ጷግሜ ክራሞት

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 26 ቀን 2018 ዓ.ም. ባሉት ጊዜያት እረፍት ላይ ቢሰነብትም፣ የ2017 ዓ.ም. የመጨረሻዋን ወርኃ ጷግሜን ያሳለፈው ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ የውክልና ሥራዎቹን በማከናወን ነበር። ይኽች የዓመቱ የመጨረሻ የእንደራሴ ዕትምም፣ የእንደራሴዎቹን የጷግሜ የመራጭ-ተመራጭ ክንውኖች፣ በ‘የክልሎቹ አዋቅራ ቀርባለች። ከዚኽ በተጨማሪም፣ እንደራሴዎቹ ዓመቱን እንዴት ከረሙ ስትል፣ እንደራሴዎቹ በዓመቱ ከከወኗቸው አንኳር ጉዳዮች መካከል፣ አንዱን የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድን ውሎ እና ዋንኞቹ ያለቻቸውን የጸደቁ ሕግጋት አጠቃሎ ይዛለች።

# የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ

የኢፌዲሪ እንደራሴዎች፣ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ሳምንት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ዋናው የውክልና ሥራ እንደመሆኑ፣ እንደራሴዎቹ ወደ 'ምርጫ ወረዳዎቻቸው በመሄድ የወከሏቸውን የማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን የመስማት ተግባራቸውን፣ ከነሐሴ ወር በመቀጠል በወርኃ ጳጉሜም ከውነዋል።

## ድሬዳዋ ምን አነሳች?

በወርኃ ጳጉሜ የመጀመሪያው ቀን፣ በድሬዳዋ የአሰሊሶ ክላስተር ስር በሚገኙ ቀበሌዎች ሲካሄድ የቆየው የሕዝብ ውክልና ሥራ የማጠቃለያ የውይይት መድረክ ተካሂዷል። በመድረኩም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የድሬዳዋ ተወካዩ የተከበሩ አብዱልጃሀድ መሀመድ ባደረጉት ንግግር፣ በክላስተሩ በሚታዩ አሥተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በማኅበረሰቡ ተወካዮች የተነሱት ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸው መሆኑን ጠቁመው፣ እንደአገር እየተሰራ ያለው የልማት ሥራ የአሁን ወቅት ችግራችንን የሚፈታ ብቻ ሳይሆን ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። እንደራሴው፣ በቀጣይም በኅብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አሥፈጻሚ አካላት እና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንደሚደረግ ገልጸዋል። ሌላይኛው የድሬ ዳዋ ተወካዩ የተከበሩ ዶ.ር. ቢፋቱ መሐመድ፣ በክላስተሩ ማኅበረሰብ ሲነሱ ከነበሩ ጥያቄዎች መካከል የተፈቱ መኖራቸውን ገልጸው፣ በተለይም ትምህርታቸውን የጨረሱ ወጣቶች በአሥተዳደሩ ባሉ የመንግስት እና የግል ተቋማት ውስጥ ሥራ እንዲፈጠር ተደርጓል ማለታቸውም ተዘግቧል፡፡ እነዚኽ ኹለቱም እንደራሴዎች የተገኙበት፣ የውክልና ሥራ መጠናቀቁን በተመለከተው መድረክም፣ በከተማ አሥተዳደሩ በተለያዩ ደረጃዎች በተካሄዱ የሕዝብ ውክልና የውይይት መድረኮች ከማኅበረሰቡ ተወካዮች ጋር ጠቃሚ ውይይት ማካሄዳቸው ተጠቅሷል። በተለይም ከትምህርት ጥራት ጋር ተያይዞ በእውቀት የሚመራ ትውልድ ለማፍራት 'የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ' በመፍጠር የትምህርት ልማትን የማሻሻል ሥራዎች በመሠራት ላይ እንደሚገኙ ተብራርቷል ተብሏል። ይኽን መሰል በሆነው እና ዶ.ር. ቢፋቱ በተገኙበት መድረክ፣ የድሬዳዋ አሥተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ ሀርቢ ቡህ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የኹለቱም የምክር ቤት አባላት ለአሥተዳደሩ ካቢኔ አባላት የሚያደርጉት ድጋፍ እና ክትትል ተጠናክሮ መቀጠሉ የሚበረታታ መሆኑን እና አሥፈጻሚው የተሻለ ሥራ እንዲሰራ አቅም መፍጠሩን መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።




በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በቢዮ አዋሌ ክላስተር ስር በሚገኙ ቀበሌዎች፣ የምክር ቤት አባሏ የተከበሩ ወ/ሮ ቢፋቱ መሐመድ ፣ የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት የክላስተሩ ተመራጮችና አመራሮች በተገኙበት የመራጭ ተመራጭ የማጠቃለያ መድረክ ባካሄዱበት ወቅት

# ኦሮሚያስ ምን ምን ጉዳዮች አሳሰቡኝ አለች?

በወርኃ ጿጉሜ የመጀመሪያው ዕለት ወደ ምዕራብ ሐረርጌ ዞን የደረሱት እንደራሴው የተከበሩ ጁሀር መሀመድ፣ ጉብኝቱን ከወረዳ አመራሮች ጋር በመሆን ያደረጉ ሲሆን፣ በምልከታቸውም፣ በዶባ ከተማ አሥተዳደር ማዘጋጃ ቤት እና በወረዳው ጤና ጣቢያ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያለው ማሻሻል የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰዋል ተብሏል። ይኽ ለውጥ በኹሉም የከተማ አሥተዳደር ማዘጋጃ ቤቶች እንዲኹም በወረዳ የገጠር ቀበሌዎች አሥተዳደር ውስጥ ማስፋት እንዳለበት ሲያሳስቡ፤ ከዚያ ባለፈም እንደራሴው እና የክልል ምክር ቤቱ አባላት፣ ለአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ አድርገዋል። በዚሁ ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ዶባ ወረዳ፣ እንደራሴው እና የክልል ምክር ቤቱ አባላት ከወረዳ አመራሮች ጋር የማጠቃለያ የውይይት መድረክ አካሂደዋል ተብሏል።

በዚያው ዞን ወደ ምሥራቁ ክፍል የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ቢፍቱ ሀሰን በተገኙበት፣ በበጎ አድራጎት የተገኘ የትምህርት አጋዥ ቁሳቁሶች ተበርክቷል ተብሏል። ከዚኽ ባአልፈም፣ እንደራሴዋ ከክልሉ ተወካይ ጋር በመሆን የደኖ ሆስፒታልን የጎበኙ ሲሆን፣ በሆስፒታሉ የባለሙያዎቹ እና የመድኃኒት እጥረት በመኖራቸው ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት እንደሚገባ የአካባቢው ኅብረተሰብ ጥያቄ አንስቶ እንደነበር ሰምተናል። ወደዚኹ የተጠቀሰው ዞን ለተጓዙት የተከበሩ እስክንድር አልይ፣ የዝናብ እጥረት ያገጠማቸው ቆላማ ወረዳዎች ትኩረት መሻት፣ የኑሮ ውድነት እና የሸቀጦች ዋጋ ንረት፣ የመድኃኒት አቅርቦት፣ የመንገድ ዝርጋታ፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነት እና የንጹሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦት የሚሉት ርዕሰ-ጉዳዮች፣ ከተወያዮቹ ከተነሱላቸው ችግሮች መካከል የሚጠቀሱት ነበሩ።



የኢፌዲሪ የ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና የቢሾፍቱ ከተማ ተወካይ የተከበሩ ዶ.ር. ለማ አበራ ጨምሮ የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባላት በጋራ በመሆን የከተማዋን ነዋሪዎች ሲያወያዩ

በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ባሌ ዞን በተካሄደው የመራጭ ተመራጭ የውይይት መድረክ የተገኙት እንደራሴዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሳዲያ አማን፣ የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባል እና የወረዳው ከፍተኛ አመራሮች፣ የመንግስት አካላት ከሕዝቡ ጋር በመተባበር በአስቸኳይ ሊፈቱ በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ጥልቀት ውይይት አድርገዋል ተብሏል። ወደ ሸዋ መለስ ስንልም፣ በምሥራቅ ሸዋ ዞን ቢሾፍቱ ከተማ በተካሄደው የውክልና ሥራ፣ ለከተማዋ ተወካዩ እንደራሴው ዶ.ር. ለማ አበራ፣ በከተማው በርካታ ተስፋ ሰጪ የልማት ሥራዎች እየተሰሩ ስለመሆኑ የከተማዋ ነዋሪዎች ገለጸውላቸውል። ዶ.ር. ለማ፣ ከኅብረተሰቡ ለተነሱ ሐሳቦች እና ጥያቄዎች ማበራሪያ እና ምላሳቸውንም ሰጥተዋል ሲል የምክር ቤቱ ዘገባ ያትታል። ወደዚያው ዞን በቀጣዩ ቀን መራጮቻቸውን ሊያወያዩ ለሄዱት እንደራሴው የተከበሩ ሹሚ አያኖ እና የጨፌ ኦሮሚያ አባሉ ሙሐመድ ከማል፣ አሁንም በየአካባቢው ታጥቀው የሚንቀሳቅሱ ኃይሎች የፖለቲካ አላማቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲያራምዱ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባ ገዳዎች፣ ሃዳ ሲንቄዎች እና የሃይማኖት ተቋማት የድርሻቸውን እንዲወጡ ተወያዮቹ አንስተውላቸዋል ተብሏል። በምዕራብ ሸዋ ዞን ለተገኙት የተከበሩ ወ/ሮ አዲሷ አሰፋም ተመሳሳይ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ተነስተዋል ተብሏል። እንደራሴዋም፣ በሕዝብ ውክልና ሥራዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ሲነሱ የቆዩ የግብርና ሥራ አፈፃፀም፣ የምርት ግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት እና የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን በተመለከተ ውይይት መደረጉን ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል። በዚኹ ዞን ውስጥ ወደሚገኘው አደአ በርጋ ወረዳ ብቅ ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ መስከረም ኃይሉ፣ ከመራጮቻቸው ጋር ባከሄዱት ውይይት፣ የሙገር ከተማ የመጠጥ ውኃ ችግር በከተማው መኖሩ፣ ከተማው በሁለት ፋብሪካዎች መካከል እያለ ለከተማው እየተሰራ ያለው የልማት ሥራ በቂ አለመሆን እና የልማት ተነሺዎቹ ለችግር እየተጋለጡ ስለሆነ በደንብ የሚደገፉበት ሁኔታ ቢመቻች ሲሉ የወረዳው ነዋሪዎች ጥያቄዎቻቸውን አቅርበውላቸዋል ተብሏል። ወደዚኹ ምዕራብ ሸዋ ዞን የማኅበረሰቡን አኹናዊ ጥያቄ ለመስማት የሄዱት እንደራሴው የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ጎንፋ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ መንግሥት የልማት ጥያቄዎች የሆኑትን ትምህርት እና ጤናን ለመመለስ ዘላቂ ሰላም አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። ወደ ሰሜን ሸዋ የአብቹ እና ኘዓ ወረዳ የተሻገሩት የተከበሩ ወ/ሮ ፋኖስ ሃይሉ እና የክልሉ ምክር ቤት አባላት፣ በሕዝቡ የተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች የወረዳ አሥፈፃሚ አካላት ማብራሪያ እንዲሰጡ ከማድረጋቸው ባለፈ፣ በክልል እና በፌደራል ደረጃ የሚፈቱትን ለይቶ በመያዝ አፈጻጸማቸውን እንደሚከታተሉ ገልጸዋል ተብሏል።



የኢፌዴሪ የ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልና በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ባሌ ዞን ጎሎልቻ ወረዳ በቡሪያ ታዳጊ ከተማ ተወካይ የተከበሩ ወ/ሮ ሳዲያ አማን፣ የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባል እና የወረዳው ከፍተኛ አመራሮች ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ሲወያዩ

ወደ ጅማም ስንሻገር፣ የተከበሩ ወ/ሪት ፈይማ ሼ/ጀማል፣ ባለፉት ጊዜያት ከወከለን ሕዝብ ጋር በልማት እና በመልካም አሥተዳደር፣ በሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች ዙሪያ እየተወያየን ቆይተናል ማለታቸው ሲደመጥ፤ በዚያው ዞን ለውክልና ሥራ በተገኙት የተከበሩ ካሊድ አባመጫ ሐጅ መሪነት በተደረገው ውይይት፣ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት የሰላም እና ጸጥታ ጉዳይ በዞንኑ እና በወረዳው በአስተማማኝ ደረጃ ላይ መሆኑ ተነግሯል። እንደራሴው ካሊድ አባመጫም፣ የተነሱት ጥያቄዎች እና አስተያየቶች የወረዳ አሥፈፃሚ አካላት ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ በክልል እና በፌደራል ደረጃ የሚፈቱትን ለይቶ በመያዝ ክትትል እንደሚያደርጉ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። በዚያው ጅማ ዞን ለተመሳሳይ ሕገ-መንግሥታዊ ክነውን ለተገኙት የተከበሩ አቶ ፈይድ ሸራብ፣ የሰኮሩ ወረዳ ነዋሪዎች፣ የመጠጥ ውሃ ቅርበት፣ የኤሌክትሪክ እና መንገድ መሠረተ ልማት እንዲኹም የቆላ ዝንብን ለመከላከል የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው መፍትሔ እንዲሰጡበት ሲሉ መጠየቃቸው ተዘግቧል። ወደ አርሲ ዞን ያመሩት እንደራሴዋ የተከበሩ ወ/ ሮ ጫልቱ ወርጅ ቱኬ በበኩላቸው፣ በተደጋጋሚ በፌዴራል እና በክልሉ መንግስት ሲነሱ የነበሩ የመንገድ ፣ የመብራት፣ የንጹሕ መጠጥ ውኃ ተደራሽነት እና የፕሮጀክት ጥራት ክትትል የሚሹ መሆኑን ጠቅሰው፣ በመልካም አሥተዳደር ዙርያ የለውን ችግር የወረዳው አሥተዳደር እና የሚመለከታቸው አካላት ከሕዝቡ ጋር በመሆን በትኩረት እንዲሰሩ ሲሉ አሳስበዋል። በዚያው አርሲ ዞን ጎሎልቻ ወረዳ የተገኙት የተከበሩ ኢሳ ቦሩ፣ የወረዳው ኅብረተሰብ ያነሳቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ገልፀው፣ መንግስት አቅሙ በፈቀደ መጠን ለሕዝቡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት እንደሚኖርበት መግለፃቸው ተዘግቧል። እዚያው ዞን የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ዛራ ቢፍቱ እና የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባላት ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ሲወያዩ፣ የወረዳው ኅብረተሰብ ያነሳቸው ጥያቄዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በማንሳት፣ መንግስት ከኅብረተሰቡ ለተነሱት ጥያቄዎች በሂደት ምላሽ እንደሚሰጥ አስረድተዋል ሲል የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ዘገባ ጠቅሷቸዋል። ከመሠረተ ልማት ጋር ተያይዞ የዲላ ሀሮ ዋጬ አስፓልት መንገድ መጓተት፣ የሀሮዋጬ-ሻኪሶ አስፋልት መንገድ እና የሜኤ ቦኮ-ቡሌ ሆራ መንገድ ሥራ አለመጀመር የተሰማበት መድረክ ደግሞ የተካሄደው፣ ጉጂ ዞን ወስጥ የተከበሩ ዶ.ር. ፍራኦል ኡዴሳ በተገኙበት የመራጭ-ተመራጭ መድረክ መሆኑ ተዘግቧል። በመድረኩ የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባላት ወ/ሮ ጫልቱ ቱቃ እና አቶ ተሰማ ዱሎን ጨምሮ ከተለያዩ ቀበሌዎች እና ከከተማ አሥተዳደሩ የተወጣጡ ባለድርሻ አካላት ሲገኙ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ አመራር ሰጭነት የዘመናት የግብርና ግብዓት ማነቆ የሆነን የማዳበሪያ ፋብሪካ የተጀመረበት እና የካሉብ የተፈጥሮ ጋዝ ወደ ምርት ለመግባት የተቻለበት የአገር ዕድገት ማሳያዎች መሆናቸው የተነገረው ደግሞ፣ የተከበሩ ዶ.ር. ከፈና ኢፋ በተገኙበት የሰሜን ሸዋው የውክልና መድረክ እንደነበር ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ሊበን ጩቃላ ወረዳ የሕዝብ ውክልና ሥራቸውን የከወኑት የተከበሩ ጫላ ለሚ ሲሆኑ፣ ሕዝቡ ያነሳቸው መሠረታዊ የልማት ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ ምላሽ እንዲሚሰጣቸው ገልጸዋል ተብሏል። ከሰላምና ፀጥታ አኳያ የመንግስት ቀዳሚ ትኩረት መስክ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በትኩረት ይሰራል ሲሉ አብራርተዋል። በዚያው ዞን ግራር ጃርሶ ወረዳ ለደረሱት የተከበሩ ወ/ሮ ብርቄ ዘውዴ እና የተከበሩ አቶ ጀቤሳ ሙላቱ፣ ተወያዩ ማኅበረሰብ የሰላም እና ጸጥታ ጉዳይን፣ የፍቼ ከተማ የሰብስቴሽን ግንባታ መዘግየትን እንዲኹም ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ጎጃም የሚሄደው መንገድ ደረጃ አለመሻሻል የሚሉት ካነሳላቸው ጥያቄዎች ዋንኞቹ መሆናቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ ዘላቂ ሰላም አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ የተነሳው ደግሞ፣ የተከበሩ ወ/ሮ ታፈሰች ሙለታ ምዕራብ ሸዋ ዞን ጉደር ቶኬ ኩታዬ ወረዳ ላይ በተደረገው የመራጭ ተመራጭ የውይይት መድረክ እንደነበር ተዘግቧል። ወደ ምሥራቅ ሸዋ ዞን ለተጓዙት ለሌላይኛዋ እንደራሴ የተከበሩ ወ/ሮ አልማዝ ወዳጆ ደግሞ፣ የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚደረገውን ጥረት ለማስፋት የመብራት ተደራሽነት ችግርን መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እንዲፈታላቸው የውይይት መድረኩ ተሳታፊዎች ጠይቀዋል ተብሏል።

በኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ ዞን ቃቄ ምርጫ ክልል የዳሌ ዋበራ እና የሰዲ ጨንቃ ወረዳዎች ነዋሪዎች በበኩላቸው፣ ቢጀመሩም ለዓመታት የተጓተቱ ፕሮጀክቶች እና እስከ አሁን ያልተመለሱ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ጥያቄዎች እንዲመለሱ ሲሉ በዚያ ለተገኙት የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ ማንሳታቸው ተዘግቧል። በ ሞጆ ከተማ አሥተዳደር በተካሄደው የመራጭ ተመራጭ ውይይት ደግሞ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊ ጉዳዮች እና የመልካም አሥተዳደር ሥራዎች በአጀንዳነት ቀርበው በስፋት ውይይት ሲካሄድባቸው፣ በመድረኩ የተገኙትም የተከበሩ ወ/ሮ አዲስ አለማየሁ ነበሩ ተብሏል። ወደ ጅማ የተሻገሩት የተከበሩ ዶ.ር አብድሰመድ ሁሴን በበኩላቸው፣ ከ70 በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች የደብተር እና የመማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ በግላቸው ከማድረጋቸው ባለፈ፣ የነገ አገር ተረካቢ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ጠንክረው በመማር ራዕያቸውን እውን እንዲያደርጉ ሲሉ መልእክት አስተላልፈዋል ተብሏል፡፡ እኚሁ እንደራሴ በጉማይ ወረዳም ተገኝተው፣ የኅብረተሰቡ የመሠረተ ልማት እና የመልካም አሥተዳደር እና የልማት ጥያቄዎች በአጭር እና በረዥም ጊዜ ምላሽ እንዲያገኙ በትኩረት ይሠራል ብለዋል ተብሏል። ወደ ባሌ ዞን ሮቤ ከተማ የተጓዙት የተከበሩ ኡስታዝ ካሚል አልይ በበኩላቸው፣ በየካቲት 2017 ዓ.ም. የሕዝብ ውክልና ውይይት ላይ፣ ከኅብረተሰቡ ለተነሱ ጥያቄዎች በተጨባጭ የተሰጡ ምላሾች እንዲኹም እስካሁን በምክር ቤት የተከናወኑ ሥራዎች ዙሪያ ለውይይቱ ተሳታፊዎች ማብራሪያ መስጠታቸውን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ዘገባ ጠቅሷል። በምሥራቅ ወለጋ ዞን የሳስጋ ወረዳ ነዋሪዎች፣ ሲያነሱት የነበረው የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ በመሆኑ መንግስትን ማመስገናቸው የተነሳበት የመራጭ-ተመራጭ መድረክ የተካሄደው ደግሞ፣ የተከበሩ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ እጅጉ በተገኙበት መድረክ እንደሆነ የምክር ቤቱ ዘገባ ሲጠቅስ፤ ሌላይኛዋ እንደራሴ የተከበሩ ወ/ሮ ፅጌ ደንቦባ፣ መንግሥት የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ ዘላቂ ሰላም አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑን አንስተው፣ ኅብረተሰቡም ለሰላም ዘብ መቆም እንዳለበት ማሳሰባቸውን ሌላው የምክር ቤቱ ዘገባ ያሳያል።

በምዕራብ ሀረርጌ ዞን፣ በበዴሳ ምርጫ ጣቢያ ኦዳቡልቱም ወረዳ እና በበዴሳ ከተማ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ምረቃን ምክንያት በማድረግ ደማቅ ሥነ-ሥርዓት መካሄዱ የተዘገበው ደግሞ፣ የተከበሩ ሲ/ር አሚራ መሀመድ በተገኙበት ሲሆን፤ የተከበሩ አቶ ወጌ ቁፋና በበኩላቸው፣ በሻሸመኔ ከተማ በኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና በፓለቲካዊ ጉዳዩች ዙሪያ የመራጭ ተመራጭ ውይይት አድርገዋል ተብሏል። በአርሲ ዞን ሙኔሳ ወረዳ ከሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር የተወያዩት የተከበሩ ወ/ሮ ማርታ ለማም፣ ከዚህ ቀደም በሕዝብ ሲነሱ ከነበሩት ጥያቄዎች መካከል ምላሽ ያገኑ መኖራቸውን ገልፀው፣ ከሠላም እና ጸጥታ ጋር በተያያዘ መንግስት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል ብለዋል ተብሏል። በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን በሰዮ ኖሌ ወረዳ ከኖሌ ካባ ቁጥር 2 ምርጫ ክልል የተውጣጡ ሴቶች ከምክር ቤት አባሏ የተከበሩ ወ/ሮ ደስታ በፍቃዱ ጋር በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መወያያታቸውም የወርኃ ጷግሜ የኦሮሚያ ክልል አንዱ የመራጭ ተመራጭ መድረክ ክንውን ነበር፤ በዚያ ውይይት ላይም፣ የሴቶች ተሳትፎ ለአገር ግንባታ፣ ለሠላም እና ለእድገት አስፈላጊ መሆኑን እና ያለ ሴቶች ተሳትፎ ልማት እንደማይገኝ በሰፊው ውይይት ተደርጓል ተብሏል።



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ ደስታ በፍቃዱ እና የጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባላት በጋራ በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ወለጋ ዞን በሰዮ ኖሌ ወረዳ ከኖሌ ካባ ቁጥር 2 ምርጫ ክልል ከተውጣጡ ሴቶች ጋር ሲወያዩ

# ወደ ቤኒ ሻንጉል ጉሙዝ

ይኽች የእንደራሴ የዓመቱ የመጨረሻ ዕትም በሸፈነችው ወርኃ ጿግሜ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ወደ ድንበረተኛዋ ክልል ቤኒ ሻንጉል ጉምዝም ተጉዘው የውክልና ሥራቸውን አከናውነዋል። ወደ ክልሉ ቡልድግሉ ወረዳ የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ጸዳለ አበራ፣ በወረዳው የተፈጠረውን ሰላም በማጠናከር እና ክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ጸጋ ተጠቅሞ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ እንደሚገባ ተናግረዋል ተብሏል። ወደ አቡራም ክልል ለሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ መናሂል ኢምራን ደግሞ፣ በወረዳው ውስጥ በሚገኙ አራት ቀበሌዎች ላይ በረዶ እና ንፋስ ቀላቅሎ በጣለው ከባድ ዝናብ መኖሪያ ቤታቸው እና ሰብላቸው የወደመባቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማጽናናታቸው ሲሰማ፣ የጉዳቱ ሰለባ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በአፋጣኝ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ጥሪ አድርገዋልም ተብሏል።

በክልሉ ዋና ከተማ ለሄዱት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙባረክ ኤልያስ፣ ተወያዮቹ፣ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት ዋጋ መጨመር እና በወረዳው የሚገኙ የጤና መድህን ተጠቃሚዎች የመድኃኒት አቅርቦት ችግሮችን በተግዳሮትነት እንዳነሱላቸው የምክር ቤቱ ዘገባ ያመለክታል። እርሳቸውም፣ ከለወጡ መንግስት ወዲኽ የመራጭ ተመራጭ መድረክ ላይ የሚነሱ የማኅበረሰብ ጥያቄዎች ላይ ትኩረት በመስጠት እየተሰራ ነው ብለዋል ተብሏል፡፡ በክልሉ ዲዴሳ ወረዳ የምትገኘው የጨሎ ክላስተር፣ በተለያዩ ውጤታማ የቡና ዘር ምርት፣ የፍራፍሬ፣ የምግብ እህል እና የቅባት ምርት የምትታወቅ እና ከፍተኛ የመልማት አቅም ያላት መሆኗ የተገለጸበት የውክልና ሥራ ደግሞ የተካሄደው፣ በተከበሩ ዶ.ር. አብድሰመድ ሁሴን አማካኝነት ሲሆን፣ እንደራሴውም የተጀመረው የልማት አቅጣጫ መቀጠል እንዳለበት እና የተነሱ ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እንዲመለሱ እንደሚሰራ ቃል ገብተዋል ተብሏል።



በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ቡልድግሉ ወረዳ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ ጸዳለ አበራ ከወከሉት ማኅበረሰብ ጋር የመራጭ ተመራጭ መድረክ ሲያካሂዱ።

## ከአፋር የተሰማው

ከጥቂት ወራት በፊት፣ በክልሉ ውስጥ ባጋጠመው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ የደረሰበት የከሰም ስኳኣር ፋብሪካ፣ በወርኃ ጷግሜ ከተጎበኙት ፋብሪካዎቹ መካከል አንዱ ነበር፡፡ ወደ ፋብሪካው የተጓዙት የተከበሩ ወ/ሮ ፋጡማ አሊ፣ በአደጋው አብዛኛው የፋብሪካው ግንባታዎች እና የመብራት ሰብስቴሽን ላይ ጉዳት መድረሱን አረጋግጠዋል ተብሏል፡፡ ወደ ክልሉ ኤሊዳአር ወረዳ ብቅ ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ አሲያ አብዱልቃድር፣ ከሕዝቡ የተነሱ የልማት፣ የመልካም አሥተዳደር እና የማኅበራዊ አገልግሎት እንዲኹም የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በየደረጃው ለሚገኙ አሥፈፃሚ አካላት እንደሚያቀርቡ ቃላቸውን ለተወያዮቹ ሰጥተዋል ሲል የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል፡፡


## አማራ ክልልስ ምን ተነሳ?

በወርኃ ጷግሜ በአማራ ክልል የተካሄደው የውክልን ሥራ አንድ ብቻ ሲሆን፣ ያም የተከናወነው በተከበሩ አባተ አረጋ መሆኑን እንደራሴ ተረድታለች፡፡ የተከበሩ አባተ አረጋ እና የክልሉ ባለሥልጣናት በተገኙበት የለጋምቦ ወረዳ እና አቀስታ ከተማ አሥተዳደር የመራጭ ተመራጭ መድረኩ፣ ከተወያዮቹ የተነሱትን ጥያቄዎች በየደረጃው ለሚገኙ አሥፈፃሚ አካላት እንደሚያቀርቡ እና መፍትሔ እንዲሰጣቸው ክትትል እንደሚያደርጉ ተናግረዋል ሲል የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል፡፡

እንደራሴውም በዚኽ የደቡብ ወሎ ዞን የውክልና ሥራቸው ወቅት፣ ለተፈናቃይ ወገኖች እና ዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አደርገዋል ተብሏል፡፡ እንደራሴው፣ ድጋፉ በዚኽ የሚወሠን ሳይሆን ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል፡፡



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የተከበሩ ወ/ሮ ፋጡማ አሊ፣ እና የአፋር ክልል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ አሲያ ከማል በዱለሳ ወረዳ የመራጭ ተመራጭ መድረክ በጋራ ሲያወያዩ፡፡



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሉ የተከበሩ አቶ አባተ አረጋ ለተፈናቃይ ወገኖች እና ዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ሲያደርጉ፡፡

## ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል . . .

ከላይ እንደተጠቀሱት ክልሎች ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያም በተጠናቀቀው ዐሥራ ሦስተኛ ወር ያካሄደችው የውክልን ሥራ አንድ ብቻ እንደነበር ከምክር ቤቱ ያሳባሰብነው መረጃ ይጠቁማል። ይኸን ሕገ-መንግሥታዊ ክንውን ዳውሮ ዞን ውስጥ የከወኑትም የተከበሩ ወ/ሮ አስቴር ከፍታው ሲሆኑ፣ እንደራሴዋም፣ የሴቶችን ተሣትፎ እና ተጠቃሚነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ገልጸዋል ተብሏል። የመድረኩ ተሳታፊዎች በበኩላቸው የኑሮ ውድነት ቅነሳ፣ የሥራ አጥ መብዛት፣ እንዲኹም የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች እና የውሳኔ ሰጪነት ሚና ተረጋግጦ በሴቶች ተጠቃሚነት ዙሪያ በቀጣይ በልዩ ትኩረት እንዲሰራም ጠይቀዋል ተብሏል።

## ሲዳማ ክልል መራጮች ምን አሉ?

በወርኃ ጿግሜ፣ እንደ ቀደሙት ክልሎች ኹሉ ነጠላ የውክል ሥራ በተካሄደባት ሲዳማ ክልል፣ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች መነሳታቸው ተዘግቧል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ በተመራው በዚኹ የመራጭ ተመራጭ መድረክ፣ ሕዝቡ እንዲፈታለት ባነሳው የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ላይ አሥፈፃሚ አካሉ ምላሽ እንዲሰጥ ለወረዳ እና ለዞን አመራሮች ግብረ መልስ ሰጥተዋል ተብሏል።
ያሳያል።



የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና በሲዳማ ክልል ማዕከላዊ ዞን በዲባ ምርጫ ክልል ተወካይ የተከበሩ ሰሎሞን ላሌ ከወረዳና ከዞን አመራሮች ጋር ሲወያዩ

# እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ወርኃ ጿግሜን ያሳለፉት፣ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነታቸው የሆነውን የውክልን ሥራቸውን በመተግበር ብቻም ሳይሆን፣ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ለአመራሮቹ እና ሠራተኞቹ ሥልጠና በመስጠትም ነበር።

በዕለተ-ጿግሜ በተካሄደው ይኸው የ የቡድን ግንባታ፣ የተግባቦት እና ግለሰባዊ ክህሎት ሥልጠና ማጠናቀቂያ ላይ የተገኙት፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሐፊ ተወካይ ከረዩ ባናታ፣ ሥልጠናው ራሳችንን የምናሻሽልበት መሆን አለበት ሲሉ ተናግረዋል ተብሏል። አቶ ከረዩ አክለውም፣ ይኽ የጿጉሜ ወቅት ለመጪው ዓመት በግል ሕይወታችንም ሆነ ለተቋማችን የተሻለ ሥራ ለመሥራት የምናቅድበት እና ሥልጠናውም ለዚኽ ዝግጅት እንደሚያግዘን አምናለሁ ሲሉም ገልፀዋል። ሥልጠናውን የሰጡት የምክር ቤት አባል የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. ከበደ ገነቴ፣ አእምሮአችን ሥራውን በአግባቡ ይሰራ ዘንድ ክፍት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋልም ተብሏል። አክለውም ከሰለጠንን የተሻለ እውቅት ይኖረናል፤ ይኽም የተሻለ አረዳድን ይፈጥርልናል፤ እሱንም ወደ ተግባር በመቀየር አመርቂ ውጤትን ማምጣት እንችላለን ሲሉ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ይጠቁማል።

# የብሪጅ ዓመታዊ አጭር ዳሰሳ

## እንደራሴዎቹ ዓመቱን እንዴት ከረሙ?

ለኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ 2017 ዓ.ም. ብዙ ክንዋኔዎች የተከወኑበት ዓመት ነበር። የተመረጡበት ጊዜ ሊጠናቀቅ አንድ ዓመት ብቻ የሥድስተኛው ዙር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላቱ፣ በተጠናቀቀው ዓመት በዛ ያሉ ሕግጋትን ሲያወጡ፤ ርዕሰ-መንግሥቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድንም ለሦስት ጊዜያት ወደ አዳራሹ ጠርተው ምላሽ እና ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል ባሏቸው ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የፌደራሉን መንግሥት አቋሟ ች አድምጠዋል። ይኽች የእንደራሴ የዓመቱ የመጨረሻ ዕትምም፣ በቀደሙት ሥድስት ዕትሞች ሽፋን ያልሰጠቻቸውን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩን አንድ መድረክ እና ከጸደቁት ሕግጋት መካከልም ዋንኞቹ ናቸው ያልናቸውን አምስት ሕግጋት እና ዋንኛ ድንጋጌዎቻቸውን እንደሚከተለው በወፍ በረር አጠናክራቸዋለች፤

በዚኹ ዓመት ውስጥ፣ ከመጋቢት

እስከሰኔ ወራት ድረስ እንደራሴዎቹ ያጸደቋቸውን ሕግጋት አስመልክቶ፣ ከዚኽ በቀደሙትን የእንደራሴ ኅትመቶች ሽፋን ተስጥቷቸዋልና 'ነርሱኑ ይመለከቷል።

የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ያለፈውን በጀት ዓመት ያሳለፈው ሥራ በዝቶበት ነበር። እንደራሴ እንዳሰባሰበችው መረጃ፣ በሳምንት ኹለት ጊዜ ማክሰኞ እና ሐሙስ ሊያደርጋቸው የሚገባቸውን ኹሉንም መደበኛ ስብሰባዎች ባያከናውንም፣ በአጠቃላይ 43 መደበኛ ስብሰባዎችን እና ሦስት ልዩ ስብሰባዎችን አካሄዷል። በዚኹ ዓመት ለምክር ቤቱ 56 ረቂቅ አዋጆች የቀረቡ ሲሆን፣ ሠላሳ አራቱ ለቋሚ ኮሚቴዎች ተመርተው ይፋዊ የሕዝብ ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ጸድቀዋል። ለምክር ቤቱ ከቀረቡት ረቂቅ አዋጆች መካከል ዐሥራ አምስቱ ወደ ኹለተኛ ንባብ ተሸጋግረው መጽደቃቸውን መረጃዎቹ ይጠቁማሉ። ከዚኽ ባለፈም፣ እንደራሴዎቹ ዘጠኝ ረቂቅ አዋጆችን ከ2017 ዓ.ም. ወደ 2018 ዓ.ም. ሲያሸጋግሩ፣ ከተሸጋገሩት መካከልም ኹለት ረቂቅ አዋጆች ከ2016 ዓ.ም. ወደ 2017 ዓ.ም የተላለፉ እንደነበሩ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ሎሚ በዶ ባለፈው ሐምሌ ወር ለእንደራሴዎቹ ባቀረቡት ሪፖርት ጠቁመዋል። ምክር ቤቱ በአዲሱ ዓመት መርምሮ ያጸድቃቸዋል ተብለው ከሚጠበቁ አዋጆች መካከል፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን የሚመለከተው እንደሚገኝበትም እንደራሴ ተረድታለች።

# የጠቅላዩ የጥቅምት ውሎ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ፣ በቀደመው ዓመት ለሦስት ጊዜያት ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብቅ ሲሉ፣ ቀዳሚው ውሏቸው ጥቅምት 21 ቀን 2017 ዓ.ም. ነበር። ‘የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ፖሊሲ እና መርህ ከኹሉም አገራት ጋር በትብብር መሥራት ነው’ ሲሉ በዚያ ዕለት የተደመጡት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በኃይል አማራጭ ሳይሆን በጋር በመሥራት የአገርን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ እንደሚቻል ለእንደራሴዎቹ አብራርተዋል፡፡ በምክር ቤቱ 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የታደሙት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ኢትዮጵያ ከአጎራባች እና መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ጋር በትብብር እና ሰጥቶ በመቀበል መርህ በመሥራት የአገሪቱን ዕድገት ለማፋጠን ጽኑ አቋም እንዳላት ሲናገሩም ተደምጠዋል።



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ ማብራሪያ በሰጡበት እለት

በዕለተ ኀሙስ በምክር ቤቱ የተገኙት ርዕሰ-መንግሥቱ፣ ‘ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር ወደ ጦርነት ልትገባ ትችላለች’ በሚል ስለሚቀርቡ ስጋቶችም ምላሽ ሲሰጡ፤ አንዳንድ ሰዎች ይኽን ጉዳይ ከኤርትራ ጋር እንደሚያያዙት፤ ሌሎች ደግሞ ሌሎች አገራት ኢትዮጵያን ሊወሩ ይችላሉ የሚል ስጋት እንዳላቸው ጠቁመዋል። ከኤርትራም ይኹን ከጅቡቲ፣ ከሶማሊያም ይኹን ከኬንያ፣ ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት ሰላማዊ ጉርብትና እንደሆነ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በስም ላልጠቀሷቸው አገራት፤ ከእንግዲህ ወዲያ ኢትዮጵያን እየመዘበሩ እና በሰፈር እያባሉ መኖር እንደማይቻል ማስጠንቀቂያ አዘል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። በዚኽ ብቻ ያላበቁት ጠቅላዩ፣ ‘እኛ ቅጥረኞች አይደለንም፤ ለሆነ ቡድን ተቀጥረን፣ በስሙ ተገዝተን፣ የሆነ ቡድን አጀንዳ የምናራግብ ቅጥረኞች ሳንሆን አርበኞች ነን፤ ይሄን አምኖ ካከበረ ማንኛውም አገር ጋር በከፍተኛ ደስታ አብረን መስራት እንፈልጋለን’ ሲሉም ተሰምተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በዚያ የምክር ቤት ማብራሪያቸው፣ ‘ሶማሊያ አካባቢ መስከን፣ መረጋጋት፣ ብሔራዊ ጥቅም ማስቀደም እንዲችሉ ጊዜ ሰጥተናል፤ እንታገሳለን፤ ቀልብ እንዲገዙ እንታገሳለን፤ ግን ኢትዮጵያ የማይናወጥ ብሔራዊ ጥቅም አላት፤ ዓለም ዛሬ ይስማ፤ የቀይ ባህር አክሰስ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ኢትዮጵያ ያስፈልጋታል’ ሲሉ ጠንከር ባሉ ቃላት የአገራቸውን አቋም አስታውቀዋል። ይኽንን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ወይ እኛ፣ ወይ ልጆቻችን ያሳኩታል ሲሉ የተደመጡት ዐቢይ፤ ሆኖም ይኽን አስታክኮ ውጊያ ይነሳል በሚል ለሚሰጉ ሰዎች፣ በኢትዮጵያ በኩል የመዋጋት ፍላጎት የለም ሲሉ አበክረው ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የምትፈልገው ሰላም መሆኑን የተናገሩት ዶ.ር. ዐቢይ፣ ከዚያ የከፋ ነገር ካልመጣ በስተቀር በኤርትራ ወንድሞቻችን ላይ ምንም ነገር አይፈጸምም ሲሉ ለእንደራሴዎቹ ቃላቸውን ሰጥተዋል፤ ጠቅላዩ አክለውም፣ ጅቡቲን እንኳን እኛ ልንረብሽ እና ልንነካቸው ቀርቶ፣ የሚነካቸው ካለ አንቀመጥም ሲሉም ተደምጠዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ክቡር አምባሳደር ታዬ አፅቀስላሴ፣ መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም. ለሕዝብ ተወካዮች እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ያደረጉትን የመክፈቻ ንግግር አስመልክቶ፤ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ፖለቲካዊ ርዕሰ-ጉዳዮችንም አንስተው ነበር። በአገር ቤት ፖለቲካዊ ኹኔታ ዙሪያ የመንግሥታቸውን አቋም ሲያብራሩም፣ የትጥቅ ትግል መሠረቱ መፈራረጅ እና ጥላቻ ስለሆነ ታጣቂዎች ከኃይል ይልቅ ሰላማዊ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ተደጋጋሚ ጥሪ መደረጉን ገልጸዋል። የትጥቅ ትግል ባለፉት ስልሳ እና ሰባ ዓመታት አገራችንን በኢኮኖሚ ወደ ኋላ እንድትቀር ጉልህ ሚና መጫወቱን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ይኽንን ምዕራፍ ለመቋጨት ሰላማዊ አማራጭን ለፈለገ ታጣቂ መንግስት ምንጊዜም በሩ ክፍት ነው ሲሉ የመንግሥታቸውን የሰላም ጥሪ አስተጋብተዋል። (የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ሌሎቹን ኹለት የዓመቱን የምክር ቤት ማብራሪያዎች፣ የመጋቢትን እና የሐምሌን የእንደራሴ ዕትሞችን ይመለከቷል)።

# ዋንኞቹ ሕግጋት

ባሳለፍነው 2017 ዓ.ም. ከጸደቁት ሕግጋት መካከል፣ በምክር ቤቱ ውስጥ ሞቅ ያሉ ክርክሮች ተደርገውባቸው ከነበሩት ሕግጋት አንዱ፣ የከተማ መሬት ይዞታን አስመልክቶ ለእንደራሴዎቹ ቀርቦ የጸደቀው ዐዋጅ ነበር። በትግበራ ሂደት የተለያዩ ችግሮች ገጥመውታል ያለውን እና ከየካቲት 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ የነበረውን የከተማ መሬት ይዞታ ዐዋጅ በመሻር፣ የከተማ መሬት ይዞታ እና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባ በሚል የተሻሻለ ርዕስ የወጣው ይኽ ዐዋጅ፣ በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ኹሉም ከተሞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ሲል የተፈፃሚነቱን ድንበር ያሰምራል። ከተማ የሚለውም፣ ጠቅላይ ዐቃቢ ሕግ በሰጠው አስተያየት መሰረት መሻሻሉን ሲጠቅስም፣ ኹለት ሺ እና ከዚያ በላይ ሰዎች የሚኖሩበት እና ከግማሽ በላይ የሚሆነው የሰው ኃይልም ከግብርና ውጪ የተሰማራ መሆን እንዳለበት ደንግጓል። ይኽ የከተማ መሬት ይዞታን የተመለከተ ማሻሻያ ዐዋጅ፣ በኹሉም የአገሪቷ ከተሞች ይፈጸማል ብሎ እንደማዘዙ፣ ይኽን ተፈፃሚነቱን ለመተግበር፣ ሊገጥሙት ከሚችሉት ችግሮች ምናልባትም ዋንኛው የሆነውን የከተሞችን አሥተዳደራዊ ድንበር ጉዳይም አንስቶ ነበር። ሰነዱም፣ የከተማው አሥተዳደራዊ ወሰን መስመራዊ ካርታ ተዘጋጅቶለት አስቀድሞ መጽደቅ አለበት ሲል ደንግጓል። ከዚኽ ባለፈም፣ የከተማውን አስተዳደራዊ ወሰን ያገናዘበ፣ በሕግ አስገዳጅነት ያለው የከተማ ፕላን መጽደቅ እንደሚኖርበትም አስቀምጧል። በአንድ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠፈር ውስጥ በሚገኙ ይዞታዎች ላይ የነበረን መብት በመደዳው ማረጋገጥ የተሰኘውን እና ረቂቁ ሥልታዊ ዘዴ ያለውን የይዞታ ማረጋገጥ ሂደት ወጪን፣ መንግሥት ቢሸፍንም፣ ይኽ ግን ለአንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነም ዐዋጁ ይጠቅሳል። ይኸው ዐዋጅ ለእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሲቀርብ፣ ከምክር ቤቱ አባላት በኩል ጥያቄዎችም ተነስተውበት ነበር። “የይዞታው ባለንብረት፣ በመሬቱ ጉዳይ እስከምን ድረስ ሊሄድ ይችላል የሚለው ግልጽ በሆነ መንገድ ሊቀመጥ ይገባል” የሚል ቅሬታን እንደራሴዎቹ ሲያነሱ ተስተውሏል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በ2017 ዓ.ም. ካጸደቃቸው ዐዋጆች ውስጥ የጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ መንግስት ተግባራዊ ካደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ጋር በቀጥታ የተገናኙ ዐዋጆች ይገኙበታል። በታኅሣሥ 2017 ዓ.ም. የጸደቀው የባንክ ስራ ዐዋጅም ለዚኽ ማሳያ ይሆናል። በ2000 እና በ2011 ዓ.ም. የወጡትን የባንክ ሥራ ዐዋጆችን የሻረው የባንክ ሥራ ዐዋጅ ለእንደራሴዎቹ የቀረበው ሰኔ 2016 ዓ.ም. ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት የባንክ አገልግሎትን ለውጭ ባለሀብቶች የሚከፍት አብይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በነሐሴ 2014 ዓ.ም. ተግባራዊ ማድረጉን ተከትሎ የተዘጋጀው አዲሱ ዐዋጅ፤ ለትውልደ ኢትዮጵያውያን የሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው የሚል ጥያቄ ተነስቶበት ነበር። ጥያቄውን ያነሳው፣ በዚኹ ዐዋጅ ዙሪያ በተካሄደው አስረጂ የውይይት መድረክ ላይ ማብራሪያዎቹን ያቀረበው፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ ጉዳዮች ጥናት ዳይሬክቶሬት እንደነበር ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የዐዋጁ የትርጓሜ ክፍል፣ ‘የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ ማለት ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ አገር ዜጋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሕጋዊ መታወቂያ ያለው ሰው’ መሆኑን ያብራራል። እንደ ውጭ ዜጋ መስተናገድ ፍላጎት ያላቸው ትውልደ ኢትዮጵያዊያን፣ በአዲሱ ዐዋጁ ላይ የውጭ ዜጎችን የሚመለከቱ ዐንቀጾች በጠቅላላ ተግባራዊ እንደሚሆኑባቸውም ዐዋጁ በጸደቀ ዕለት ሲነገር ተስተውሏል። የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ ስለሚሳተፉበት ኹኔታ የሚዘረዝረው የዐዋጁ ክፍል፣ በአንድ ባንክ ውስጥ የውጭ ዜጎች የሚይዙት አጠቃላይ የአክስዮን መጠን ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከ49 በመቶ መብለጥ እንደማይችል ገደብ አስቀምጧል። በዐዋጅ መሠረት፣ የውጭ ዜጎች በአንድ ባንክ መዋዕለ-ንዋያቸውን ማፍሰስ የሚችሉት በቀጥተኛ የውጭ መዋዕለ ንዋይ አማካኝነት በውጭ አገር ገንዘብ ብቻ መሆኑን የሚጠቅሰው ዐዋጁ፣ የውጭ ዜጎች በእያንዳንዱ የሒሳብ ዓመት መጨረሻ ከአክሲዮን ባለቤትነት የሚያገኙትን የትርፍ ድርሻ በኢትዮጵያ ብር መልሰው በመዋዕለ-ንዋይነት ፈስሰ ሊያደርጉ እንደሚችሉም ዐዋጅ ደንግጎ ጸድቋል።

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በተጠናቀቀው ዓመት ካጸደቋቸው ሕግጋት መካከል በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ሌላይኛው ዐዋጅ፣ አጠቃላይ የትምህርት ዐዋጅ የተሰኘው ነበር። የትምህርት ጥራትን፣ ፍትሓዊነትን መሰል እሴቶችን ለማረጋገጥ አስቻይ ኹኔታን የሚፈጥር ሕግ ባለመኖሩ በሚል መነሾ በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት የተዘጋጀው፣ የአጠቃላይ ትምህርት ዐዋጅ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ያዛል። ይኸው ዐዋጅ፣ አንድ ተጨማሪ የአገር ውስጥ ቋንቋ ከፈደራል የሥራ ቋንቋዎች መካከል የተማሪ ወይም የወላጅ ምርጫን ታሳቢ በማድረግ እንደ አንድ ትምህርት ዓይነት ከ3ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ይሰጣል ማለቱ፣ ምክር ቤት አባላት በኩል ብርቱ ትችት ገጥሞትም ነበር። እንደራሴዎቹ፣ አምስት የፌደራል ቋንቋዎች ገና ሳይጸድቁ፣ ይኽን ሐሳብ የትምህርት ዐዋጅ ውስጥ ማካተቱ ተማሪዎች የትኛውን የፌደራል ቋንቋ እንዲመርጡ እንደተፈለገ በግልጽ አያስቀምጥም ሲሉ ተደምጠው ነበር። የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንደ ትምህርት ዓይነትነት እና ማስተማሪያ ቋንቋነት ከቅድመ-አንደኛ ደረጃ ጀምሮ እንዲሰጥ የሚያዘው ዐዋጁ፣ መቆሚያውን የክፍል ደረጃ ግን ክልሎቹ እንዲወስኑ ሥልጣን ይሰጣል። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቻ መማር ተማሪዎች ሥራ በሚቀጠሩበት ወቅት ከፌደራል እና ዓለም ዓቀፍ ቋንቋዎች ጋር ተግባብተው እንዳይሰሩ ያግዳቸዋል ሲሉ ይኽንን የዐዋጁን ሐሳብ የተቃወሙ እንደራሴዎች በበኩላቸው፣ በዚኽ የተነሳም ዐዋጁ ግልጽ መደረግ አለበት ሲሉ ጠይቀው ነበር። ከዚኽ ባለፈም፣ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ከሚያውቁት አካባቢ ወደ ሩቅ ቦታ በመወሰድ መፈተን፣ ተማሪዎቹን ለተጨማሪ ጭንቀት የሚዳርግ በመሆኑ መሻሻል የሚችልበት ዐንቀጽ በዐዋጁ ሊካተት ይገባል ሲሉም፣ እንደራሴዎቹ መጠየቃቸው ተዘግቦ ነበር። ከዚኽ በተጨማሪም፣ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የመምህራን ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅምን በተመለከተ የማሻሻያ ዐንቀጽ በዐዋጁ ሊታይ እንደሚገባም አባላቱ ጠይቀው ነበር ተብሏል።

በዚኽች እንደራሴ የዓመቱ የመጨረሻ ዕትም፣ ወደኋላ መለስ ብለን ልንጠቅሳቸው ከምንችላቸው ዐዋጆች መካከል፣ በአራት ተቃውሞ እና በአንድ ድምፀ-ተዓቅቦ የጸደቀው የንብረት ታክስ ዐዋጅ ይገኝበታል። በአብላጫ ድምጽ የጸደቀው ይኽ ዐዋጅ፣ በረቂቅ ደረጃ ከነበረበት ጥቂት ማሻሻያዎች ተደርገውበት እንዲጸድቅ የእንደራሴዎቹ ፈቃድ ሆኗል። ማሻሻያ ከተደረገባቸው ድንጋጌዎች መካከል የንብረት ታክስ በመቶኛ የሚከፈልበት ዋጋ መሠረት፣ በየዓመቱ የሚደረገው የንብረት ታክስ ጭማሪ እና በታክስ ነጻ ስለተደረጉ የቦታ እና የሕንጻ አገልግሎቶችን የሚመለከቱት ይገኙበታል። በረቂቅ ደረጃ የነበረው ዐዋጅ፣ ታክስ የሚከፈልበት ዋጋን በተመለከተ ያስቀመጠው ትርጓሜ ላይ ተጨማሪ አዲስ ንዑስ አንቀጽ እንዲጨምር መደረጉን እንደራሴ ባደረገችው አጠር ያለ ዳሰሳ ተረድታለች። ከዚኽ ባለፈም፣ በሥድስት ክፍሎች እና በ43 ዐንቀጾች የተከፋፈለው የንብረት ታክስ ረቂቅ ዐዋጅ፣ የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎችንም ይጠቅሳል። ዐዋጁ፣ በ1968 ዓ.ም. የወጣውን የከተማ ቦታ ኪራይ እና የቤት ታክስ ዐዋጅን እንዲሁም በ1971 ዓ.ም. የወጣውን የእዚህኑ ማሻሻያ የሻረ መሆኑ ተስተውሏል። በተጠናቀቀው ዓመት አጋማሽ ላይ በጸደቀው በዚኹ ዐዋጅ፣ በ1986ቱ ዐዋጅ 'የከተማ ቦታ ኪራይን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች' ባሉበት እንደሚቀጥሉ ሰፍሯል። የከተማ ቦታ ኪራይን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች እንዲሻሩ ያልተደረገው ደግሞ፣ 'ከተሞች ከሊዝ ውጪ ባለ ነባር ይዞታ ላይ የከተማ ቦታ ኪራይ የሚሰበስቡት በዚኽ ዐዋጅ መሰረት በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ለእንደራሴዎቹ ቀርቦ የነበረው ማብራሪያ አትቷል።

የከተማ መሬትን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው ማሻሻያ ዐዋጅ መጽደቅም እንዲኹ፣ የ2017 ዓ.ም. ዋንኛው የእንደራሴዎቹ ክንውን ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የቀረበው ይኽ ዐዋጅ፣ ከተሞች ሙሉ ለሙሉ ወደ ሊዝ ሥርዓት እንዲገቡ እና የሊዝ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ በመላ አገሪቱ በሚገኙ ከተሞች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይኽ ማሻሻያ ዐዋጅ ማስፈለጉን ይጠቅሳል። በ2004 ዓ.ም. የጸደቀውን፣ የከተማ ቦታን ስለመያዝ የወጣውን ዐዋጅ ይተካል የተባለው ይህ ማሻሻያ ዐዋጅ፣ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ለሚነሱ ነባር ባለይዞታዎች የሚሰጡ ምትክ ቦታዎች ወደሊዝ ሳይቀየሩ በነበሩበት እንዲቀጥሉ ፈቅዷል። ሌላይኛው አንኳር ከተሜ ተኮር የዐዋጁ ነጥብ፣ አዲስ አበባን ጨምሮ በብዙ ከተሞች የሚስተዋለውን የመንግሥት እና የግል ይዞታዎች በጉርብትና መገኘትን አስመልክቶ ያስቀመጠው ማሻሻያ ነው። የመንግሥት እና የግል ባለይዞታ ቤቶች በአንድ ቁራሽ መሬት ላይ በንጽጽር ካርታ የሚተዳደሩ ይዞታዎችን፣ አብላጫ ወደ ያዘው ባለይዞታ በምደባ እንዲካተት እንደሚደረግም ዐዋጁ አዟል። ለዚኽም ሆነ ለሌሎቹ ማሻሻያዎች አዲስ የዐዋጅ ሃሳብ ነው የተባለውን ‘ምድባ’ የተሰኘውን የሕግ ሂደት ሲያወሳም፣ በጨረታ ሊስተናገድ ለማይችል ተቋም የከተማ መሬት በሊዝ ይዞ ማልማት የሚፈቅድበት ስልት እንደሆነም ፍቺ ይሰጣል። በዚህ የምደባ ስልት የከተማ መሬት በሊዝ እንዲሰጣቸው ከተፈቀደላቸው መካከልም፣ በፌደራል መንግሥቱ ሥር የሚገኙ ባለበጀት የመንግሥት ተቋማት ይገኙበታል ተብሏል። በጨረታ እና በምደባ ሊተላለፉ በማይችሉ እና አገራዊ ፋይዳ ብሎ ዐዋጁ ለጠራቸው አገልግሎቶች የሚጠየቁ የከተማ መሬቶች ድርድር በተሰኘው ሌላኛው አዲስ የተሰኘ የሕግ ማዕቀፍ እንደሚተላለፉም ሲደነግግ፣ በዚህ የድርድር ሂደት የከተሞቹን መሬት የሚያገኙት እነማን እንደሆኑም ይዘረዝራል። በድርድር መሬት እንዲያገኙ ዐዋጁ ከፈቀደላቸው መካከልም፣ የኢንዱስትሪ ልማት ጥያቄዎች፣ ባለኮከብ ሆቴሎች እና ሪዞርቶች፣ ዐዋጁ ግዙፍ ብሎ የጠራቸው የሞል ፕሮጀክቶች እና በመንግሥት እና በግሉ ዘርፍ በሽርክና የሚካሄዱ የከተማ መልሶ ማልማት ፕሮጀክቶች ይገኙበታል ተብሏል። የከተማ መሬትን በሊዝ መያዝ የሚቻለው በምደባ፣ በጨረታ አልያም በድርድር ብቻ መሆኑን የሚደነግገው ይኸው ዐዋጅ፣ ከዚኽ ውጪ የከተሞችን መሬት መያዝን ይከለክላል። ዐሥራ ሦሥት ዓመታት ያስቆጠረው ነባሩ ዐዋጅ፣ የከተማ ቦታ በሊዝ እንዲያዝ የሚፈቀደው በጨረታ ወይም በምደባ ስልት ብቻ እንደነበር ይታወሳል። ሌላይኛው ዐዋጁ የአዲስ አበባ ከተማን አስመልክቶም ኹለት አኹናዊ የመሰሉ ነጥቦችን ያነሳል። በአዲስ አበባ ከተማ የቀበሌ መኖሪያ ቤት ሕጋዊ ተከራይ በልማት ሲነሳ የጋራ መኖሪያ ቤት በግዢ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻችለታል የሚለው ይኸው ማሻሻያ ዐዋጅ፣ የተከራየው ቤት የንግድ ቤት ከሆነ ደግሞ፣ ምትክ ቦታ እንደሚሰጠው ካልሆነም የመሥሪያ ቦታ በሊዝ ስሪት እንደሚሰጠው ያዛል።

## እንደ መደምደሚያ. . .

ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ፣ በሌሎቹ የእንደራሴ ዕትሞች ሽፋን የሰጠናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራት የከወነው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ዓመቱን ያጠናቀቀው በዚኽ መልኩ ነበር። ከእነዚኽ በሕገ-መንግሥቱ ከተጣሉበት ኃላፊነቶች መካከልም፣ ቁጥራቸው የበዛ የፌደራሉን መንግሥት የበጀት ተቋማት ከሥድስት እስከ ዘጠኝ ወራት የረዘሙ ተቋማዊ ሪፖርቶቻቸውንም ገምግሟል። ምላሽ ያስፈልጋቸዋል ያላቸውን አንኳር የተቋማቱን የአፈፃፀም ጉድለቶችንም ያርሙ ዘንድ ጠበቅ ያሉ ማሳሰቢያዎችንም ሲሰጥ ሰንብቷል። ከዚኽ ባለፈም፣ በዓመቱ አጋማሽ የካቲት ወርን ጨምሮ፣ በወርኃ ነሐሴም ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ የውክልና ሥራዎችን ተግብሯል። እነዚኽ የውክልን ሥራዎች ምን ጉድለት እንደነበረባቸው እና በቀጣዩ ዓመት በምን መልኩ ጉድለቶቹ መሸፈን እንደሚችሉ በሚለው ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ሰፋ ያሉ የ‘ራስ በ‘ራስ ምክክሮችን ጨምሮ፣ ለአባላቱ የተለያዩ የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችንም ሰጥቷል። ለአገሪቷ ይበጃሉ ያላቸውን በዚኽ መልኩ በወፍ በረር ያየናቸውን ክንውኖች የከወነው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ከ2017 ዓ.ም. ያሻገራቸውን ሕግጋት ጨምሮ፣ በቀጣዩ ዓመትም ሌሎች በኹነኛ መልኩ የአገሪቷን ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ይወስናሉ ተብለው የሚገመቱ ሕግጋትን ያወጣል ተብሎም ይጠበቃል። በተለይም፣ ዓመቱ የምርጫ ዓመት ከመሆኑ ባሻገር፣ የእንደራሴዎቹ መሰናበቻም ነውና፣ ቀጣዩ 2018 ዓ.ም. ለእንደራሴዎቹ የበረታ ጊዜ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

# እንደራሴ

እንደራሴ በብረጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል፡፡

## ከራስ ውርድ፦

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.